# ከራስ ጋር ጨዋታ (ክፍል 2)

የሕይወት ትርጉሙ መላ ቅጡ ጠፍቶን
መከራ ስቃይን በአለና አጅቦ መታቀፉ ቀንቶን
የአፄውም አርባ አራት
የደርጉ አስራ ሰባት
ዘረኛ አስራ ዘጠኝ
ሁሉንም መሸከም ሳይባልም በቃኝ
ዕድላችን ሆኖ ነጋ ጠባ ስቃይ
እምቢኝንም ትቶ እሺን እየደገምን
ከብር--አልባ ምርቃና በቁማችን ሞተን
የሕይወት ትርጉሙ በባዶ አለና
መብት አልባ መኅተት ጠፍቶ ሰብዕና
ጎርፉ ከቶ ማይቆም ማያስብልም ቀና
ህይወት በሌሌበት በባዶ አለና።

----

እስከመቼ ማለት የጅል ቋንቋ ሆኖ
የመድረኩ አንበሳ የሩቅ ሀገር ፋኖ
ደሙን የገበረው ሞኝ እየተባለ
ጀግንነት ትርጉሙ ሳንሞት ቀለለ።
የዝንቦች ክፍለ ጦር አንዲት መሶብ ላይከፍት
በአፋዊ ጥይት አንድም ጠላት ላይሞት
ተመክሮ ሞልቶ በደም የተገኘ
አወቅኩ ነቃሁ ያለው አውቆ እየተሞኘ
የእንብርክኩ ኑሮ ህይወት ገላጭ ሆኖ
በባዶ አለና እስከመቼስ ከቶ?
አስራ ዘጠኝ ዓመት ሀገር ስትዋረድ
አስራ ዘጠኝ ዓመት ህዝባችን ሲበደል
ስልጡን ፖለቲካ ስህተት መደጋገም
ከትግል ርቆ ጎራዴ መነቅነቅ
ጠላት ወዳጅ ላይሆን ነጋ ጠባ ታቅፎ
ትግል በልመና አይሎና ገኖ
መስሎ መኖር ብልጠት መኖርም መበርከት
የባዶ አለና ሕይወት አልባ ውርደት።

-----------------------

ተራ ሚሉት ቋንቋ ራሱ ተራ ነው
ድህው ምኑ ተራ ክቡር ሰው እንጂ ነው፡፡
ልሂቅ ነን ልዩዎች የተመረጥን ምሁር
ባለፈረንጅ ዲግሪ ዶክተር በሉን ክቡር
የሚሉት በዙና መድረኩንም ይዘው
አባይ ቀላጤዎች የሰው ባዶ ሆነው
ሁሉም ነገር ግራ በችሀ በቸሆ
ነገሩ አልጫ አቴሆ ባቴሆ
ወፍ ቋንቋ ለወፍም ከቶም የማይገባ
መቀለጃ ሆነ ትግልም ተናቀና፡፡
አፍ ምላስ ክላሺን ቁጭ ብሎ ዘመቻ
አዋጊው ዘረጠ ሚሞት ሳይዋጋ ፡፡
ኑሮም ተባለና መከራን መግፋቱ
ብልጠት ተባለና ብትን ቃል መድገሙ
ኑሮ ከተባለ መቃብር መሞቁ
መከራ ደቁሶን ቀኑ ጨልሞብን
አለና አንላለን ማጠፊያው አጥሮብን፡፡

------------------

በመለየት ጭንቀት የሚመዘን ፍቅር
በጎን ቆማ እያለች የጠፋች ስትመስል
የፍቅር ትርጉሙ መቸ ደስታ ብቻ
ስጋትም  ፍርሀትም በቀን በጨረቃ
ሲበዛ ሲጣመም ቅናትም ዘው ብሎ
ጤና የነበረውን ራሱን አስቶ
ወደ ወንጀል ገፍቶ
ጭራሽ አሳብዶ
ልብ እያበረረ ቀልብ ያልነውን ነጥቆ
ጉድ አድራጊ ፍቅር ስሙን አለሳልሶ፡፡
ፍቅር በያይነቱ አለ የጠለቀ
ከሴት ወንዱም አልፎ ሀገር ያስወደደ
በአንድም ሳይወሰን ሕዝብን ያስመረጠ ፡፡
የሚያሳብድ ስሜት ለትግል የሚጠራ

ሞት አይፈሬ አድራጊ ጋባዥ ለፈተና።
ፍቅርን መጀመሪያ ሕዝብን መውደድ ካልነው
ሁሉን በላይ ፍቅርን ሀገር መውደድ ካልነው
ሆድ አፍቃሪነትን ማነው ቦታ የሰጠው
ራስ መውደድንስ ማን ቀዳሚ አረገው?
ቅቤስ ጠባሽነት በማን ክብር ተሰጠው?
የፍቅር ትርጉሙ ይዘቱ ጠፍቶብን
አለና እንላለን ልብ ያልነው ሞቶብን።

------------------

ነፍሴን ሂጂ ብዬ ህሊናንም ወግድ
ተመሳስሎ ኑሮን አቅፌ ልነጉድ
ታሪክን ሰርገፎ ብረዛን አቅፌ
በእምቢኝ እያሾፍኩ መጎንበስ መርጬ
የመጣ ይምጣ እንጂ መርህን አልሸጥም ማለትንም ትቼ
በሾሁ መካከል የሱፉን አበባ አየሁትም ብዬ
አካባቢው ገምቶ ከህደት ሲከረፋ
ሸተተኝ እያልኩኝ ሳሮን ፅጌረዳ
ማታለል ራስን ሁሌም ነጋ ጠባ
ፍርሀትን ማፈኑ ከባድ ግዳጅ ሆኖ
ሀሰትን ማቀፉ መዋረድ መድከሙ ቅሌትም ተክኖ
ነጋ ቀኑ ስንል ጎህ አልቀድ እያለን
ሁሌም ጨልሞብን አለና እንላለን።

----------

ሁሉም ተቀይሮ ቅርሳችን ተንቆ
ታሪክ  ያልነው ተረት ቃልም ወድቆ ረክሶ
ክህደት ንቃት ሆኖ ፍርሀትም ድፍረት
ጀግና የምንላቸው ሆነው ተወቃሾች ያጠራቸው ብልጠት
በአፉ የሚወሰልት የምሁር መንጋ ፈልቶ
ለድቅድቅ ጨለማ ሁሌም ተጎንብሶ
ለአረመኔ አገዛዝ ሁሌም ደፋ ብሎ
በራስ ግምት ጠቢብ ራስ አዳናቂ

የቡከኖች መንጋ መቸም አለቅላቂ
አጥንታቸው ነቅዞ በቅንዓት በውርደት
ህሊናቸው ሞቶ መረን ባጣ ክህደት
ሕዝብን እንዳይሰማ ጆሮቹ ተደፍነው
ውሻ ከትፋቱ ሆኖ የሚገልፀው
ልባምነት አልባ ቅሌት ነፍሱን ይዞት
አለና ይለናል መጥቶበት ጣረሞት፡፡

----------------

መሰዋት ትርጉሙ ዛሬ ተቀይሮ
ሚሰዋው ጊዜ እንጂ ህይወት መሆን ቀርቶ
መሰዋት ጅልነት መጋፈጥ መጨረስ በሚል ተፈርጆ
ሰማዕት ተወግዘው አታጋይ ተወግዞ
ታሪክ ተሰርዞ፤ ታሪክ ተበርዞ
ኢትዮጵያዊነትም ለድርደር ቀርቦ
ከጠላት መዋደድ እያደር መናደድ መሆኑ ቀረና
ከጠላት መፋቀር ባርነትን ማጥብቅ ብልጠት ተባለና
ዛሬም ነገ ስህተት ፈርማና ድርድር
ታሳሪ ማሩኝ ባይ ትግል አጥፊ ውዠንብር
ሰይጣን ሲጋልበው ፅድቅ እየመሰለው
የፈረንጆች ኩርኩም ልቡን እያሞቀው
ለወያኔ ሰግዶ የቆመ ሚመስለው
አስመሳዩ ታጋይ ሕዝብን ጉድ አረገው ፡፡
የዕብዱ ማደሪያ ቤት የወፈፌው ሆኖ
ነጋ ጠባ ከማጥ ሳለ ተመክሮ ፡፡
የሰው ቁስል አይነዝር ምንጊዜም አይጎዳ
አለና ማለቱም የአዞ እንባ ለበጣ ፡፡

---------------

ለዓይን አጥር ጠፋና መታወርም ከብዶ
ግፍ በግፍ እያዩ ወይ ነዶ ወይ ነዶ
ለቁራጫም ኑሮ ከውልደት እስከሞት
ተጨራምቶ ኑሮ ተቀምቶ ሕይወት
አለሁ አለሁ ባዩ የምስጡ ክፍለ ጦር
ክልል አንድን አልፎ ተስፋፍቶ በሀገር
ጥሬ ስጋ በዪው ሰውም አልምር ብሎ

ግፍ በግፍ እያዩ መቃጠል ወይ ነዶ
የበቃኝ ድራሹ፣ የእምቢኝም አቅጣጫ
የጠፉንም መስሎ የትግሉ መነሻ፣ የትግሉ መድረሻ
የህፃን ልጅ ዳዴ መቆም ግን የነገ
ቢጠበቅ ቢጠበቅ ቀን አልወጣ እያለ
በቀቢፀ ተስፋ ፯ ብትን ብሎብን
በታኝ ተበታኙ አንጃውም ፈልቶብን
ማይታሰብ ሆኖ ቃል ኪዳን ማፍረሱ
የማይሆን ሆኖብን ለነፍጥ መጎንበሱ
አልዋጥ እያለን ሕዝብ ሀገርን መክዳት
ኑልኝ ብትለን ግን ወግኟ ልንላት
ለውዲቷ ሀገር ሁሌም አለን አልናት ፡፡

-----------

ዛሬማ ሌላ ነው ጊዜ ተለውጧል
ዛሬማ ልዩ ነው ሰዉም ሌላ ሆኗል
ቃላትም ወግ ይዘው ትርጉም ቀይረዋል
ሽንፈት ድል ተብሎ መፍረክረክም ፅናት
ከሀዲው ማንዴላ በአንዲት ወር እስራት
ከፎቅ መፈጥፈጡ ሳያናይድም መዋጥ
ሞት አይፈሬ መሆን በፋሺስት ላይ መትፋት
የትላንት ሆኑና ያጠራቸው ብልሀት
የፋራ ተብለው ራስን ማስጠቃት
ስልጡን ፖለቲካ አዲስ ቋንቋ መጥቶ
ከመሞት መሰንበት መዋረድ ተመርጦ
ጠላት ፊቱ ሲጠቁር ምህረትን ልመና
መፈረም መጎንበስ መለስ ሆይ ማረና
ሀፍረት ማቅ በሀገር ራስ አስቀብሮ
ሽንፈቱን ድል ማለት ውርደት ተከናንቦ
አለና ጫጫታ በቁሙ ተቀብሮ፡፡

------------

የእናት ሆድ ዝንጉርጉር ለምንስ ይባላል

ሰውን በወለደ ዘርን ባስቀጠለ ለምን ይወቀሳል?

እናትማ  እናት ነች ሁሌም ምትክ አልባ

ተሸካሚ ዋና የሁሉን መከራ፡፡

የሰው ልጅ ቢበላሽ ቢሆን አሳፋሪ

ህብረተሰቡ እንጂ ዋና ተጠያቂ

ስርዓቱ እንጂ ነው አውሬውን ፈጣሪ

እናትማ እናት ነች ፍቅርን አስተማሪ፡፡

የሰው ሰውነቱ በእናት ቢሆን ኖሮ

ስንት ወንጀል በጠፋ ባገር ፍቅር ሰፍኖ፡፡

ሕፃን ልጅ ሲወለድ ከማህፀን ሲወጣ

እትብቱ ሲቆረጥ ከናት መለየቱን ወዲያውን ሲረዳ

ወደ ዓለም መምጣቱን የሚያጅበው በእንባ

ምስጢር ቢያውቅ እኮ ነው የሰው ኑሮን ጣጣ

ማያባራ ለቅሶን የስቃይ አለና፡፡

-----------

ምን እሆን ነበረ አንቺን ባላገኝሽ

ምን ይውጠኝ ነበር አንቺን ባላፈቅርሽ

ሁሉን ዕውቀት ካንቺ ባልማር ባልቀስም

ደደብ ይሉኝ ነበር አንጎለ ጭልምልም?

ድፍረትሽን ካንቺ ባልዋስ ባላገኝ

ምን ይውጠኝ ነበር  ጠላት ሲፈትነኝ?

ቦ ጊዜ ለኩሉ ብለሽ ያሰተማርሽኝ

ትዕግስትም ጊዜ አለው ንዴትም እንዲሁ ብለሽ የነገርሽኝ

ባይገባኝስ ኖሮ ከመዋረድ ኑሮ ይሻልሀል መሞት ብለሽ ያስረዳሽኝ

ምን እሆን ነበር አንቺን ባላገኝሽ

ምን ይውጠኝ ነበር አንቺን ባላፈቅርሽ

ፅናት ጀግንነትን ካንቺ ባልዋስሽ?

ምን ይውጠኝ ነበር ሰዎች ቢያሾፉብኝ

ከመቃብር ገብቶ አለና ባይ ቢሉኝ?

------------

ላቡ ሲንጠባጠብ ጤዛን ካተነነ
ደሙ የፈሰሰ ዕለት ጎሁ ከቀደደ
የልቡ ትርታ የጭቁን ከሆነ
ጨለማው ሲጠና ደማቅ ኮከብ ካየ
ክብሪት እየጫረ ብርሀን ካበራየ
ሰው ነህ አንተ በሉት ሰው ነሽ አንቺ በሏት
የሕይወት ትርጉሙ ለሱ ነው የገባው ለሷ ነው የገባት::
ሞትን መፍራት ከንቱ የሰው ሚዛን ቀናሽ
ሆድን መውደድ ውርደት ሰውን አርጊ ርካሽ
ሞትን መናቅ ግሩም ህይወትን አጣፋጭ
ሰብዕናን ማስከበር የቁም ሞትን ሰራዥ::
በጊዜ አሸዋ ላይ ኮቴያችን ካልታየ
በሕይወት መዝገብ ውስጥ አሻራ ካልቆየ
ኑሮ ማለት ከንቱ እርሻ ባዶ አዝመራ
ነፍስን በድን አርጎ የምፀት አለና::

-----

ሰው ከሀገር ጠፍቶ ዲዮጋንም ሞቶ
ከራስ ጋር ጨዋታ ቀን አልፎለት ደርቶ
ያን የጠፋ ወኔን ቀን ተሌት ፍለጋ
አምርሮ ከጠፋም ደብቁ ጋጋታ::
ሀቁን ከልብ ማየት ሀሞትን ማጤኑ
ከባድ እየሆነ ራስ መገምገሙ
ጥይቷ እስክትጮህ ፉከራ ሽለላ
የቁርጥ ቀን ዕለት ሊቀድም ፍርጠጣ ::
ለምን ይወለዳል የቦቅቧቃ መንጋ
ለሀገር ከቶ ላይበጅ ሁሌም እየጎዳ?
ራስ ላይ ምርምራ ጥያቄ ከበዛ
ይቀድ ይሆን ያ ጎሕ ፍርሀት እየጠፋ
አድርባይነትም ሞቶ ላይነሳ?
ከራስ ጋር ጨዋታ ተስፋን ለመፈለግ
ነፍስ ህሊናን ነክቶ ሀቅን ለመቃረም
ውዠንብርን ገድሎ ብሩህ ቀን ለማለም ::
በሀቅም ድፍረትን ዕናትን ተላብሶ
ታሪክን ለማደስ የባዶ አለናን ከአፍ አስወግዶ::

----------

እነሱም ንቀውን እኛም ተቀብለን
መሬትም ሲነጠቅ ሀገር ስትወረር ዝምታንም መርጠን
ዘርዓይ ደረስን አብረሃም ደቦጭን ጳግም ገድለን ቀብረን
የወኔንም ትርጉም አላወቅንም ብለን
ሁሉን ተሸክመን፥ ግፉን ሁሉ ችለን
ዱርዬውም ካድሬ ጳጳስ ነኝ እያለ ልባርካችሁ ሲለን
ራስ ደፋን ወደን አንገት ሰበር ለምደን
መኖር መበርከትን ካፋችን ለጥፈን
ድክመታችን ገሀድ ሱዳንም ወረረን
ድክመታችን ገሀድ ወያኔ አዋረደን።
ማላዘን ማልቀሱ ምለላው በርክቶ
አላዋቂ መሪ ሁሉን አደናብሮ
ከሀዲው ሆዳሙ ፈሪው ባገር ሞልቶ
ህልም ራዕይ ተኖ የብሩህ ቀን ተስፋ
በጠራራ ፀሐይ ሁሉ እያንቀላፋ
ላገር ዘፋኝ ብዙ ላገር ሟች ግን ጠፍቶ
ልሙትላት ባዩም በትችት ተወርፎ
ብልጠት የተባለው ጅብና አህያን በረት አሳድሮ
ያገር ሽማግሌ ለወገን ማፈሪያ ፍፁም እንቶ ፈንቶ።
ያ ዝምታም ቢሆን ለበግም አልበጃት
ሲያርዷት ሲበልቷት አለና እያሰኛት።

--------------------

ሀገር ወዳድ ማነው ዘወትር ጥያቄ
አውጫጭኝ ይጠራ በዛብን አባዜ።
ወንዜ ተራራዬ ክብሬ ባዩ ሞልቶ
የወገኑን ስቃይ ላያነሳ ምሎ።
ሰንደቅ ዓላማዬ ፉከራው ብዙ ነው
ዘርዓይ ደረስን ማንስ ቢያስታውሰው።
ፈጣን ምላስ በዝቶ ጮሌነት አራዳ
ተመሳስሎ መኖር የአድርባዮች ካባ
ማንዴላ የተባለው ምንደኛ እየሆነ
ፍርሀትና ክህደት ብልጥነት ተባለ።
ዕንቁ የሀገር ልጆች ለሀገር የሞቱ

ጀግና የኢትዮጵያ ሀገር የወደዱ
ቆራጥ ፅኑ አንበሶች ሕዝብን ያፈቀሩ
ባረሱት መሬት ላይ በደም በእንባቸው
የቡከኖች አረም ሲጥር ሊያንሰራራ
አለና እንበለው ዘብ እኮ ቆመናል
ሀገር ወዳድ ዜጎች ዛሬም በርክተናል ።
ሕይወቴ ላገሬ ብለን እየማልንም
ለሀገር ወዳድነት እንሰጣለን ትርጉም
ለውዲቷ ኢትዮጵያ አለና እያልን።